# ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ሊያስተውሉት የሚጋባ ሐደት

(ሰርጸ ደስታ)

November 30, 2017 22:05

ሕዝብ በአደባባይ ያለማቋረጥ ራሱን ከጠላቶቹ ለማላቀቅ እየታገለ ዛሬ ሁለት ዓመት ሊሆነው ነው፡፡ ከዛ በፊት የሆነውን ሁሉ በማወቅም በአለማወቅም ብዙዎቻችን የጠላቶቻችን መጠቀሚያ ሆነናል፡፡ ከሁለት ዓመት ወዲህ ብዙዎቻችን ሳናውቅ እናተፋ ወይም እንሸወድ የነበርነው አሁን ነገሮች ገብተውን በሙሉ ልብ ወደራሳችን ተመልሰናል፡፡ ቀድሞውንም አውቀን የጠላት ጉዳይ አስፈጻሚ የሆንው ግን ከቀን ወደ ቀን ጭንብላችን እየተገፈፈ ለሕዝብም እየጠራ ነው፡፡ ሆኖም አሁንም ብዙዎች በውዥንብር እንኖራለን፡፡ አሁን ለማስተዋል በቂ መረጃዎች አሉ፡፡ የሚከተሉትን ማሰተዋሎች ወያኔና ኦነግ፡-

ወያኔና ኦነግ የጥቅም መጋራት ባይኖራቸውም ኢትዮጵያን በማፍረስ አላማ አንድ ነበሩ፡፡ ዛሬ የገባንበት አዘቅት ሁሉ የእነዚህ ሁለት የአገርና ሕዝብ ጠላት ድርጅቶች እንደሆኑ ማስተባበያ ሊሰጥ የሚችል ያለ አይመስለኝም፡፡ ሁለቱም ዋና ጠላት አድርገው የተነሱት ዛሬ አማራ እየተባለ የሚጠራውን ሕዝብ ነው፡፡ በዚህ ሕዝብ ላይ በጋራ የፈጸሙጽን አረመኔያዊ ግፍ ሲፈጽሙ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዝም ብሎ ነበር፡፡ ዛሬ እኔ አደለሁም እኔ አደለሁም በሚል እርስ በእርስ በጋራ የፈጸሙጽን በአረመኔያዊ ግፍ ሊክዱን ሳያፍሩ ያወሩናል፡፡ በደኖና አርባ ጉጉ ታሪኩ ቀላልና ቀጥተኛ ነበር፡፡ ኦነግ ይገድላል ወያኔ ይቀርጻል፡፡ ወያኔ አስገዳይ ኦነግ ገዳይ፡፡ በቃ ታሪኩ ይሄው ነበር፡፡ ጉራፈርዳ ኦነግ በአካል አለ ባይባልም ወያኔ በድጋሚ ኦነግ የፈጠራቸውን ጭፍሮች ተጠቅሞ ሁለታኛው አስከፊው አረመኔያዊ ግፍ ነበር፡፡ እነዚህ በጉልህ የሚታወቁት እንጂ ወያኔና ኦነጋውያን አማራ በተባለው ሕዝብ ብዙ ትንን ሌሎች ያልታዩ ግፎች ፈጽመዋል፡፡ ወያኔ አማራ የተባለውን በኦሮሞ በግፍ ስታስገድል ቆይታ ዛሬ ደግሞ ኦሮሞን በሱማሌ አረመኔዎች ማስፈጀት ከጀመረች ይሄው ወራቶች አስቆጥረናል፡፡ በፊት ለወያኔ ዋና የሚያስፈራት ጠላት አማራ የተባለው ሕዝብ ነበር፡፡ አሁንም ነው፡፡

ከሁለት ዓመት ወዲሕ ግን ኦሮሞ ከአማራም በከፋ ለወያኔ አደገኛ ሆኖ ታያት፡፡ በዛው ልክ ለ 25 ዓመት በሁለቱ ሕዝቦች የማይታረቅ ጠላትነት ብትሰራም ሁለቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሚስጢሩ እየገባቸውና ወንድማማችነታቸውን እያጠናከሩ መጡ፡፡ ይሄ ኦሮሞን የበለጠ ለመጥላት ለወያኔ ዋናው ምክንያቷ ሆነ፡፡ ወያኔ ጠላት ብላ መማኒፌስቶዋ ከጅምሩ የመዘገበችው ሕዝብ ጋር ለ 25 ዓመት ኦሮሞን አማራን ለመበቀል አንደሁነኛ መሳሪያ በመጠቀሙ በአጋሯ በኦነግ አማካኝነት በሁለቱ መካከል አይታረቅም ያለቸውን መርዝ ብትተክልም አልሆን አላት፡፡ ኦሮሞ በራሱ መነሳቱ ሳይበቃ ከአማራ ጋር ወንድሜ ወንድሜ ጀመረባት፡፡ እና ዛሬ ላይ ወያኔ ከአማራው ይልቅ ኦሮሞን እጅግ ትጠላዋለች ትፈራዋለች፡፡ ዛሬ በአረመኔ የሕወሀት ቅጥር ሶማሌዎች በኦሮሞ ላይ የሚፈጸመው አረመኔያዊ ግፍ ምክንያቱ ይህው ነው፡፡ የገረመኝ ግን እስከዛሬ አማራው በተባለው ሕዝብ በአረመኔ ኦነጋውያን ቅጥሮቿ ተመሳሳይ ድርጊት ስትፈጽም ሙሉ ከ 20 ዓመቶች በላይ እንዳለፉ የዘነጋንው ይመስላል፡፡ የአሁኑ የአረመኔ ሶማሌያውያን በኦሮሞ ላይ የሚፈጽሙት ቀድሞ አረመኔ ኦነጋውያን በአማራ በተባለው ላይ ሲፈጽሙት የኖረውን ራሱን ነው፡፡ ወያኔ እድሜ ከአገኘች ቀጥሎ ደግሞ ሌላ ስጋት የሚፈጥርባት ስታገኝ እንዲሁ ከሌላው ሕዝብ የምታገኛቸውን አረመኔዎች ተቀጥርበታለች፡፡ ገነዘብና መሳሪያው እንደሁ በእጇ ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ግን ሲጠቃለል ፌደራሊዝም በሚል ወያኔና ኦነግ በዘር የከለሉን እለት ነበር ይህን ግፍ እንዳቀዱልን ያልተገነዘብነው፡፡

የኦሮሞ አክቲቪስት ነን የሚሉትና ወያኔ፡-

ዛሬ እንደ ድሮው ኦነጎች ለወያኔ የዚያን ያህል ጠቃሚ አደሉም፡፡ በምትካቸው ሌሎችን አሰማርታብናለች፡፡ ልብ በሉ

አሁን ላይ የኦሮሞ አክቲቪስት ነን የሚሉትን ለመታዘብ ጥሩ እድል የተፈጠረ ይመስለኛል፡፡ አንድም ቦታ የሕዝቡ አሁን እየደረሰው ያለው ግፍ ሲሰማቸው አታዩም፡፡ በሚዲያቸው ሲያራግቡ የምትሰሙት ለሚዲያቸው ድጋፍና እይታ ልዩ ጠቀሜታ ስላለው እንደሆነ አስተውሉ፡፡ ኦሮሞ በቀዬው ይገደላል ለእነሱ ሰበር ዜና ይሆናቸዋል፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ድርጊታቸውን አስተውሉ፡፡ ጎንደሬዎቹ የኦሮሞ ደም የእኛ ደም ነው ያሉበትን ክስተትና ለዓመጣት ወያኔና አነጋውያን በሁለቱ ሕዝብ መካከል ሲገነቡት የነበረውን የጥላቻ ግንብ ድርምስምሱን እነዳወጣው ታዝበናል፡፡ በወቅቱ ለኦሮሞ አክቲቪስቶች ከወያኔ በአልተናነሰ አደገኛ ናዳ ነበር፡፡ በዛ ወቅት በቀጥታ እንደ ወያኔው ጌታቸው ረዳ ከአፋቸው ቢያወጡት ሊነቃ የኦሮሞም ሕዝብ መንግሎ ሊጥላቸው ሆነ፡፡ ሌላ ስልት መንደፍ ነበረባቸውና ብዙ የሚያስተዛዝቡ ሴራዎችን መከሩ፡፡ አንደኛ የኦሮሞ ሕዝብ እንዲህ ለወያኔ አደገኛ ሆኖ መነሳቱ ለኦሮሞ አክቲቪስቶችም መጥፊያቸው ሆነ፡፡ ይባስ ብሎ ከአማራም ጋር የአንድነት መፈክር ማንሳት ጀመረ፡፡

እንግዲህ በዛን ወቅት የሆነውን ሂደት ለማርገብ ሚስጢራው ወዳጃቸው ወያኔንም ለመታደግ ነበር የለንደኑን አገርን የመበታትን መፈክርና የአትላንታውን የኦሮሞ ቻርተር በሚል ያዘጋጁት፡፡ ልብ በሉ ኦሮሞ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ጉዳይ ኖሮት ቻርተር አስፈልጎት ነበር? ኦሮሞስ ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ነበር ኢትዮጵያዊ ማንነቱ ተመልሶ በአገር ባለቤትነትና በዋናነት እየታገለ ባለበት ወቅት አገርን ማፈራረስ ነው ብሎ መፎከር አላማውን አስተውላችኋል? አላማው ሶስት ነበር በዋናነት ኦሮሞ አንስቶት አማራ የተቀላቀለውን ትግል የአገር አፍራሾች በሚል ሕዝብን ለመፍጀት ምክንያት እንደሆናት ለወያኔ የተሰራለት ቅንብር ወያኔ ለዛ ድራማ ስንት እንደከፈለች አላውቅም፡፡ ሁለተኛው በኦሮሞና አማራ መካከል የተፈጠረውን ሕብረት ለማምከን ሶስተኛ የሁሉንም ትኩረት ከዋናው ትግል በማስወጣት ትግሉን ማቀዝቀዝና ለወያኔ ፋታ መስጠት ነበር፡፡

ከዚያ በኋላ እነዚህ አክቲቪስት ነን የሚሉት ዋና ሥራቸው የኦሮሞ ሕዝብ ከአማራው ጋር እነዳይታቅ ያልተፈጠረ ታሪክ እየፈጠሩ ማቀንቀን ሆነ፡፡ አስተውሉ ከዛን ጀምሮ በኦሮሞ አክቲቪስት ነን በሚሉትና በሚዲያቸው እየቀረቡ ያሉትን ነገሮች፡፡ የሚኒሊክ ሰፋሪዎችም ዋና አፍ ማሙዋሻቸው ሆነች፡፡ አንቺ ታቦኪያለሽ ውሻ ይደፋብሻል ሆነና ነገሩ እነሱ ይህን እንቀልፍ አጥተው ቢሰሩም ጭራሽ ሌላ የለየለት የሁለቱ ሕዝቦች ሕብረት ዛሬ አፍጥጦ መጣ፡፡ ዛሬም ግን አክቲቪስት ነን የሚለው ቡድን መሸነፍ አልፈለገም፡፡ የአማራና ኦሮሞ ሕብረት ጉድ አፈላ፡፡ ኦሮሞ አማራ ሲሰደብና ሲወነጀል ደስ የለዋል ብሎ ስለሚያምን ይሄው አክቲቪስት ቡድን ይሄንኑ ተያይዞታል፡፡

በዛው ልክ ግን ሌሎችን ለማነቅ የዘጋጀው ገመድ አንገቱ ውስጥ ገብቶ እየጠበቀበት ነው፡፡ እጣ ፈንታችሁ በእኛ እጅ ነው የሚል የተስፋ መቁረጥ ፉከራም ሰማን፡፡ እነዚህ የኦሮሞ አክቲቪስት ነን የሚሉት ሴራቸውን የሚያዛምቱበት ሚዲያ ግን እኮ የሕዝብ ገነዘብ ነው፡፡ የዚሁ ሚዲያ ሥራ አስኪያጅ ሌላውን እጣ ፈንታችሁ በእኛ እጅ ነው እያለ ወያኔን አሁንም እድሉ አለ እያለ ይመክራል፡፡ ወያኔ ግን ይቅርታ ሊደረግለት የማይችል የሕዝብና አገር ጠላት እንደሆነ ዛሬ ሕዝብ ግልጽ ብሎለታል፡፡ ወያኔን ለድርድር ለማቅረብ አደለም እኮ የዛሬው ትግል፡፡ ወያኔን ለዘመናት ራሱ ሕዝብንና አገርን ለመቅበር ሲቆፍረው የነበረው ጉድጓድ ውስጥ ለመቅበር እንጂ፡፡

የአንድነት ኃይል ነን ባዮችና ወያኔ፡–

እነዚህ ደግሞ ዋና የአገር አሳቢ ነን የሚሉ ገና ሕዝብ ብዙም ያላወቃቸው የወያኔ አጋር ናቸው፡፡ ግንቦት 7 አንድነት ንቅናቄ ምናምን ገና ብዙ ሕዝብ አልነቃባቸውም፡፡ እውነታውን እነነጨው፡፡ ወያኔ ግንቦት 7 የሚባል ድርጅት አገር ቤት እንደሌለ አሳምራ ታውቃለች፡፡ ግንቦት 7 ስሙን ለወያኔ አከራይቶ የሚኖር ድርጅት ነው፡፡ ልክ በኦነግ ሥም የኦሮሞን ሕዝብ ስተፈጅ እንደኖረችው የአማራን ሕዝብ በግ 7 ሥም እፈጀች ነው፡፡ ይልቅ አንድ ሌላ የትግሬ ቡድን ብዙ ሰራዊት ይዞ ኤርትራ ውስጥ አለ፡፡ ጉዳዩ ግልጽ ነው፡፡ አንድም ስለእሱ ወያኔ ትንፍሽ አትልም፡፡ ይህ ቡድን ተቃዋሚ ሳይሆን ወያኔ የክፉ ቀን የክት ኃይል እንደሆነ አስተውሉ፡፡ በኤርትራ ድጋፍ ኢትዮጵያን ነጻ እናወጣለን የሚሉት ድራማቸው ሳያንስ ሕዝብ አሁንም ትኩረት እንዲሰጣቸውና ከትግሉ እንዲዘናግ ይፍጨረጨራሉ፡፡ ይህን አስተውሉ፡፡ በብዙ ነገር እየተበላን ነው፡፡

የወያኔ ሹምሽርና የትግሬ ወያኔዎች እየፈጠሩት ያሉት ውዥንብር፡-

ትግሬ ወያኔዎቹ አላማቸው ስለሆነ ወሬውን ትልቅ ለማድረግ መሞከራቸው ብዙም አላስደነቀኝም፡፡ የሚገርመው የወያኔን ሹምሽር ቁምነገር አደርገው ብዙ ትልልቅ የተባሉትም ሚዲያዎች ሲያወሩት ማየት ነው፡፡ ሲጀምር እነሱ ያደረጉት የበለጠ እድሜ ሊያራዝምላቸው የሚችል ተንኮልን የሚያሴሩትን በዋናነትና በመሪነት ሥልጣን ሰጡ እንጂ አንዱ አንዱን ለመጣል አደለም፡፡ የቀድሞው ወያኔ መሪ ሚስት ተወገደች ምናምን የሚለው ወሬ በተለይ ትልቅ ጆሮ አግኝቷል፡፡ ሕዝቤ ሆይ አትሸወድ የተፈለገውም ይሄው ነው፡፡ ትኩረትን ለመሳብ፡፡ አዜብ እነድ አማራ ኦሮሞ ባለስልጣን ቃሊቲና ሌላ ማሰቃያ አደለም ቀጣዩ እድሏ እንደነ ጀነራል አበበና ጻድቃን በዘረፈቸው ገንዘብ እየተንደላቀቀች ለወያኔ ታማኝ የውስጥ አርበኛ ሆና ለመቀጠል እንጂ፡፡ ትግሬ ወያኔዎች የምለው ዋናዎቹን ሳይሆን የወያኔ ደጋፊዎቹን ማለቴ ነው፡፡ ትግሬ ወያኔዎች ታዲያ ሰሞኑን እንደተቃዋሚ ሊያደርጋቸው ይቃጣቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ ሊሆንለት የሚገባው የትግሬ ወያኔዎች በወያኔ የተሰጣቸውን ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ማስተዋል ነው፡፡ ይልቁንም ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትል ሁሉ ቀጣይ ሊያሴሩት እያሰቡ ያሉትን በትኩረት ልትከታተል ያስፈልጋል፡፡ ሳሞራ፣ አዜብ ምናምን አይምሰልህ እነሱ በውስጥ በተስማሙት ተስማምተው ነው ስብሰባ ረግጦ መውጣት ምናምን የመሳሰሉ ድራማዎችን ፊትለፊት የሚያሳዩህ፡፡ በተመሳሳይ ትግሬ ወያኔዎችን አሁን ላይ በግልጽ መደገፉ ስላላዋጣ በተቃዋሚ ጎራ በማሰለፍ ትግሉን ለመበረዝ ነው፡፡ ማንም ሰው ትግሬ ወያኔን አምኖ ቢቀበል እባብ ሞኝን ሁለት ጊዜ ነደፈው የተባለው ተሻሽሎ አባብ ሞኝን ዘጠኝ ጊዜ ነደፈው ይባላል፡፡ ይህን ስል ትግሬ ኢትዮጵያዊ እንዳለ አውቃለሁ፡፡ እነዚህ ግን በጣት የሚቆጠሩ ብቻ እንደሆኑ ለአፍታም መዘንጋት የለበትም፡፡

በመጨረሻም በወያኔ መካከል ሽኩቻ አለ ሲለን የቆየው ኢሳት እናዝናለን አላማህን ሕዝብ እየገባው አደለም፡፡  ለነገሩ የነጻድቃንንም የሴራ ጽሁፍ በበጎነት ሲተነትንልን ነበር፡፡ ኢሳት የሕዝብ ነው ማለትና ኢሳት የሕዝብን አላማ አላማዬ ባሉ ነው የመዘወረው ማለት የተለያዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ እድል መስጠት አያስፈልግም፡፡  በምትኩ ሌሎች ሚዲያዎች ለሕዝብ ወሳኝ የሆነ መረጃ እያቀበሉ እንደሆነ እናስተውል፡፡ ሕብር ሬዲዮ፣ የእስልምና ተከታይ ወገኖች የሆነው ቢቢኤን የመሳሰሉት አሁን ላይ ወሳኝ የሕዝብ ወገንተኝነታቸውን እያሳዩ ይመስላል፡፡ የመንግስት የተባሉት ቪኦኤ፣ ዶቼቪሌና ኤስቢኤስ ተቃዋሚ ከሚባሉት በብዙ እጥፍ የመንግስትን ሴራዎች በመቃወም ከሕዝብ ጎን ቆመዋል፡፡ አገር ቤት ከአዘለቀለት የኦሮሚያ መንግስት ሚዲያ በብዙ ምዕራፍ ተቀየሮ የሕዝብ አጋር የሆነ ይመስላል፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ከወረሯት ጥላቶቿ ይታደግ! አሜን!

ሰርጸ ደስታ